# ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 5ኛ ዓመት

# የ 2020 ክፍል

## 2016–2017 የመጀመሪያ ዓመት ዘጠነኛ ክፍል:-

## MCPS የመመረቂያ ተፈላጊ መስፈርቶች ባጭሩ

የሜሪላንድ ስቴት አንድ ዲፕሎማ ለሁሉም የሁለተኛ ደረጃ ተመራቂዎች ይፈቅዳል፣ በአራት መሟላት የሚገባቸው ፈርጆች ስኬታማ ክንውን ላይ በመመስረት፡ - ምዝገባ፣ የኮርስ ክሬዲት፣ የተማሪ ትምህርታዊ አገልግሎት፣ (SSL)፣ እና የሜሪላንድ ምዘና-ግምገማዎች። የምዝገባውን ተፈላጊ መስፈርት ለማሟላት ተማሪዎች ከ8ኛ ክፍል ባሻገር አራት አመታት በአጥጋቢ ሁኔታ መፈፀም አለባቸው። ሌሎች ሁሉም ተፈላጊ መስፈርቶች ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ባጭሩ ተገልፀዋል። እባክዎ ስለ 2016–2017 የ MCPS ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ኦንላይን (በይነመረብ) ኮርስ መጽሔት በዚህ ድረገጽ ላይ ይመልከቱ፡- coursebulletin.montgomeryschoolsmd.org/Home/PlanningTools ወይም የበለጠ መረጃ ለማግኘት የትምህርት ቤትዎን ካውንስለር ያማክሩ።

## የኮርስ ክሬዲቶች

| | |
|---|---|
| እንግሊዘኛ | 4 ክሬዲቶች |
| ኪነ-ጥበባት | 1 ክሬዲት ለ FA የተመደበ ሲሆን በስነጥበብ (አርት)፣ ዳንስ፣ ድራማ/ቲያትር፣ እና ሙዚቃ ስለ FA በኮርስ መጽሔት ላይ የተገለጸውን/የተመደበውን መስፈርት የሚያሟላ። |
| የጤና ትምህርት | 0.5 ክሬዲት |
| የሂሳብ ትምህርት | 4 ክሬዲቶች፤ከሜሪላንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የአልጄብራ መመዘኛ ጋር ተዛማጅነት ያለው 1 የአልጄብራ ትምህርት ወይም "አልጀብራ I" እንደ ቅድመሁኔታ ተፈላጊ የሆነበት 1 ተጨማሪ ካሬዲቶች በተከታታይ የሒሳብ ኮርሶች፣ እና ደረጃ የጠበቀ የጅኦሜትሪ ትምህርት ይዘት ጋር ተዛማጅነት ያለው 1 የጅኦሜትሪ ትምህርት።<br>በ 2018 እና ከዚያ በኋላ ለሚመረቁ ተማሪዎች የስቴት አዲስ ተፈላጊ መስፈርቶች፡- በ 2018 እና ከዚያ በኋላ የሚመረቁ ተማሪዎች በእያንዳንዱ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ዓመት በሂሳብ ኮርስ መመዝገብ አለባቸው። ይህ ለተማሪዎች መመረቂያ በሂሳብ ከ4 ክሬዲቶች በላይ ሊያስገኝላቸው ይችላል። |
| የሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርት | 1 ክሬዲት |
| ሳይንስ | 3 ክሬዲቶች 1 ባዮሎጂ ክሬዲት፣ ዴዝግኔትድ (BC) እና 1 የፊዚካል ሳይንስ ክሬዲት፣ ዴዝግኔትድ (PC) መጨመር አለበት። የበለጠ ዝርዝር ለማግኘት የሳይንስ ዲፓርትመንት የሚሰጣቸውን የኮርስ ዝርዝር ክፍል ይመልከቱ። |
| የህብረተሰብ ሳይንስ ጥናት | 3 ክሬዲቶች፣ አንድ ክሬዲት በዩ.ኤስ. ታሪክ (1 U.S. History credit)፣ አንድ ክሬዲት በዓለም ታሪክ (1 World History credit)፣ እና አንድ ክሬዲት በብሔራዊ፣ ስቴት፣ እና አንድ ክሬዲት የአካባቢ መንግስት አመራር (1 National, State, 1 Local Government) ተፈላጊ ነው። |
| የቴክኖሎጂ ትምህርት (TE) | 1 ክሬዲት ለ.TE.የተመደበ። ይህን መስፈርት ለማሟላት የተመደቡ ኮርሶች በኮርስ መጽሔት ላይ ተገልጸዋል። አድቫንስድ ቴክኖሎጂ (AT) ኮርሶች የ TE ኮርስ መስፈርቶችን አያሟሉም። |

| በምርጫ የሚወሰዱ ለምረቃ የሚያስፈልጉት ተጨማሪ ክረዲቶች ከሚቀጥሉት ሶስት አማራጮች በአንዱ መሟላት ይችላሉ | አማራጭ 1 | ምርጫ 2 | ምርጫ 3 |
|---|---|---|---|
| | 2 ክሬዲቶች በዓለም አቀፍ ቋንቋ/ዎርልድ ላንጉጅ፣ የአሜሪካን የምልክት ቋንቋ ሊጨምር ይችላል እና2.5 ክሬዲቶች በተመራጭ ኮርሶች | 2 ክሬዲቶች በአድቫንስድ ቴክኖሎጂ ትምህርት (AT) እና 2.5 ክሬዲቶች በተመራጭ ኮርሶች<br>TE ኮርሶች እንደ AT ኮርስ ክሬዲት አይቆጠሩም። | በስቴት የፀደቀ የጥናት ፕሮግራምን ማጠናቀቅ እና 0.5 ክሬዲት በተመራጭ ኮርሶች |

## የተማሪ አገልግሎት ትምህርት (SSL)

| | |
|---|---|
| የተማሪ የአገልግሎት ትምህርት (SSL) | 75 የአገልግሎት-ትምህርት ሰአቶች<br>ከ 6ኛ ክፍል በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ MCPS ለሚገቡ ተማሪዎች የ SSL መስፈርት በተመዛዛኝ ይያዛል። |

## የሜሪላንድ አጠቃላይ-ሁለገብ የምዘና ፕሮግራም (MCAP)
## የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምዘና (HSA) መስፈርቶች [1,2,3,4]
## እነዚህ የመመዘኛ መስፈርቶች በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት (MSDE) አማካይነት ሊለወጡ/ሊቀየሩ ይችላሉ።

| | |
|---|---|
| አልጄብራ 1 | በአልጄብራ 1 የተገኘ የኮርስ ክሬዲት እና<br>• Algebra 1 HSA ወይም Algebra 1 PARCC ከ 2016–2017፣ አስቀድሞ መውሰድ ወይም<br>• Algebra 1 PARCC/MCAP መመዘኛ ማለፍ፣ወይም<br>• የ 2019-2020 ወይም 2020-2021 Algebra 1 MCAP መመዘኛ መውሰድ |
| እንግሊዝኛ 10 | በእንግሊዝኛ 10 ወይም እኩል ተመጣጣኝ ኮርስ ላይ የተገኘ ክሬዲት፣ ወይም በ ESOL 3 ወይም የበለጠ እና<br>• የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ/ሊተርሲ 10 (English Language Arts/Literacy 10) መመዘኛ ማለፍ፣ ወይም<br>• በ 2019–2020 ወይም በ 2020–2021 የእንግሊዝኛ ቋንቋ ስነጥበብ/ሊተረሲ " English Language Arts/ Literacy 10 MCAP" ኮርስ መውሰድ |
| የመንግስት አስተዳደር | ብሔራዊ፣ የስቴት፣ እና የአካባቢ መንግስት አመራር ወይም ተመጣጣኝ በሆነ ኮርስ የተገኘ የኮርስ ክሬዲት እና<br>• ስነ መንግስት ምዘና ማለፍ |
| ሳይንስ | በባዮሎጂ የተገኘ የኮርስ ክሬዲት፣ እና<br>• Biology HSA መውሰድ በ 2016–2017፣ ወይም<br>• Maryland Integrated Science" መመዘኛ መውሰድ |

[1]ተተኪ ፈተና፡- በተተኪ ፈተናዎች (AP/IB) ብቁ የሚያደርጋቸው ነጥቦችን የሚያገኙ ተማሪዎች በዚያ ይዘት የ MCAP HSA መስፈርትን ያሟላሉ።
[2]ክሬዲት ማዛወር፡- ከሜሪላንድ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ውጪ የሚዛወሩ ተማሪዎች አንዳንድ የ MCAP HSA ይዘት መስፈርቶችን ሲዛወሩ ባላቸው ክሬዲት ማሟላት ይችሉ ይሆናል።
[3]የተቀናጀ የፈተና ውጤት ግምገማ አማራጮች ይኖራሉ።
[4]እንደመሻገሪያ ድልድይ የሚሆን እቅድ፡- ለ MCAP HSA የመመረቂያ ብቃት መመዘኛዎችን ለማሟላት የሽግግር እቅድ አማራጭ መንገድ ነው። በመሸጋገርያ እቅድ አማካይነት፣ መደበኛውን ፈተና ማለፍ የሚያዳግታቸው ተማሪዎች ፕሮጀክቶችን በማከናወን የይዘት እውቀት ችሎታቸውን ያረጋግጣሉ/ያሳያሉ።

0197.21 • EGPS